የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

# ዲጂታል ዜና መጽሔት

ቁጥር 4

መጋቢት 2016 ዓ.ም



## የባንኩ የስድስት ወራት አፈጻጸም ጥሩ ውጤት የተመዘገበበት መሆኑ ተገለጸ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የስድስት ወራት አፈጻጸም ጥር 28 ቀን 2016 ዓ.ም በባንኩ መሰብሰቢያ አዳራሽ በተገመገመበት መድረክ አፈጻጸሙ ጥሩ ውጤት የተመዘገበበት መሆኑን የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ ገለጹ፡፡

በዚሁ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደርና ተጠሪ ተቋማት በተገኙበት በተካሔደው የግምገማ መድረክ የባንኩ አሠራር በየጊዜው እየተሻሻለ ከመምጣቱ ባሻገር የፋይናስ ቁመናው ጤናማ መሆኑን ሚኒስትሩ አረጋግጠዋል፡፡

በተለይም በግብርናው ዘርፍ ካሁን ቀደም የነበሩ ችግሮችን በማረም በበጀት ዓመቱ ከፍተኛ ውጤት የመጣበት መሆኑ የሚበረታታነው ያሉት ሚኒስትሩ በቀጣይም በሁሉም ዘርፎች ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ተቆጣጣሪ ተቋም የሆነው የመንግስት የልማት



ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ኃይለሚካኤል በበኩላቸው የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ ያሉትን አማራጮች በሙሉ መጠቀምና የባንኩን የሀብት ደረጃ ማሳደግ እንደሚገባ ገልጸዋል። አሁን ላይ ባንኩ እንደ ባህል አጠናክሮ እየሠራበት የሚገኘው የብድር አሰባሰብ ሥርዓትን ዘላቂ እንዲሆን ለማስቻል ልምዱ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደደሚገባም አሳስበዋል።



የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝደንት ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው ባንኩ በ5 ዓመቱ የስትራቴጅክ እቅዱ ያስቀመጣቸውን ዋና ዋና ሥራዎችን በመለየትና የትኩረት አቅጣጫ በማስቀመጥ መፈጸም መቻሉ ለስኬት እንዳበቃው ያብራሩ ሲሆን፣ በተለይ በብድር ማጽደቅ ረገድ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ከዘጠና ከመቶ በላይ ብልጫ ያለው አፈጻጸም መመዝገቡን ገልጸዋል፡ ፡ የብድር ስርጭቱንም በተመለከተ ከዕቅድ በላይ መፈጸሙን ያረጋገጡት የባንኩ ፕሬዝዳንት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ብልጫ ማስገንዘቡን በሪፖርቱ አረጋግጠዋል።

በተያያዘም ክቡር አቶ አህመድ ሺዴ እና ክቡር አቶ ሀብታሙ ኃይለ ሚካኤል ባንኩ የውስጥና ውጫዊ ገጽታዎቹን ሳቢና ለሥራ ምቹ ከማድረግ አኳያ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን ተዘዋውረው ጎብኝተዋል። ■




# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለቆላማ አካባቢዎችና አርብቶ አደር ማኅብረሰቦች የሚሰጠው አገልግሎት እየሰፋ ነው።





በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርና ኢጋድ (IGAD) ትብብር ከጥር 17-23 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በሚሊኒየም አዳራሽ ሲካሄድ የነበረው የምስራቅ አፍሪካ አርብቶ አደሮች ኤክስፖ በርካታ ሁነቶች የተስተናገዱበት ሆኖ አልፏል። ከእነዚህ ወሳኝ ሁነቶች አንዱ ደግሞ ‘አርብቶ አደርነት፡ የምስራቅ አፍሪካ ኅብረ-ቀለም’’ በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀው የፓናል ውይይት ነበር። ይህ የውይይት መድረክ በፓናሊስትነትና በክብር እንግድነትም ጭምር የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አቶ አህመድ ሺዴ፣ የሶማሌ ክልል ፕሬዘዳንት ክቡር አቶ ሙስጠፌ መሀመድ፣ የዓለም ባንክ ምክትል ፕሬዘዳንት ሚስተር ኦስማን ዲዮን፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንሲንግ ም/ፕሬዝዳንት አቶ አስፋው አበራ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ጉምሩክ፣ ከዓለም የምግብ ድርጅት (FAO)፣ ከዓለምአቀፋ የግብርና ልማት ፈንድ (IFAD) እና የክልል ተወካዮች የተገኙበት መድረክ ነበር።

የፓናል ውይይቱ ኢትዮጵያ ልማት ባንክ በቆላማና አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጠውን አገልግሎት ያብራራበትና በኤክስፖውም የኤግዚቢሽኑ ተሳታፊና ስፖንሰርም የሆነበት አጋጣሚ ነበር።

የፓናል ውይይቱ በአርብቶ አደሩ አካባቢ የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነትና ውስንነት፣ የገበያ ትስስር፣ ቴክኖሎጂና አጠቃላይ በአርብቶ አደሩ የልማት ጥያቄዎች ዙርያ ሐሳቦች ተነሥተዋል። በተለይም የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነትና ውስንነት በተመለከተ ከተነሡ ነጥቦች አንጻር የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንሲንግ ም/ፕሬዝዳንት አቶ አስፋው አበራ <<በእነዚህ አርብቶ አደሮች በስፋት በሚገኙባቸው ቆላማ አካባቢዎች ተስማሚ የፋይናንስ አገልግሎት ማቅረብ ተገቢ እንደሆነ ባንካችን አምኖ እየተንቀሳቀሰ ነው።>> በማለት ለቆላማ አካባቢዎችና ለአርብቶ አደሩ ማኅብረሰብ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን አረጋግጠዋል። ለዚህ እንደ አንድ ማሳያ የጠቀሱት ባንኩ በዚህ ዓመት ያስጀመረውን ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎትን ሲሆን፣ አርብቶ አደሩና ቆላማ አካባቢዎች የሚባሉት በአመዛኙ የሶማሌ ክልል፣ አፋር ክልል፣ ከፊል ኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በርካታ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ፈላጊዎች እንዳሉ ታሳቢ በማድረግም <<ዲቢኢ. ተዐውን>> የተሰኘ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎትን በስፋት ለማቅረብ ባንኩ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አረጋግጠዋል።

አቶ አስፋው አበራ በዚሁ መድረክ ያብራሩት ሌላው ወሳኝ አገልግሎት ባንኩ አርብቶ አደር ማኅበረሰቡን ለማገልገል በቅርቡ ለመተግበር

እየተንቀሳቀሰባቸው ካሉ ፕሮጀክቶች አንዱ የሆነውን የአርብቶ አደር ኢኮኖሚ አደጋ ተጋላጭነት ቅነሳና የፋይናነስ አካታችነት ፕሮጀክት (DRIVE) ነው፡፡

ይህንን ፕሮጀክት በተመለከተም ማበራሪያቸውን ያከሉት አቶ አስፋው <<ባንካችን በአርብቶ አደር አካባቢዎች ከሚመለከታቸው አካላትና ዓላም ባንክን ከመሰሉ የልማት አጋሮች ጋር ፕሮጀክት ቀርጾ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ ይህ ፕሮጀክት በዚህ በቆላማ አካባቢዎች ያሉ ማኅበረሰቦች ለአደጋ ተጋላጭነታቸውን በቀነሰ መልኩ ዘላቂ ልማት እንዲኖር ከማረጋገጥ አኳያ ምቹ የሆነ የፋይናንስ አገልግሎት ሆኖ ቀርቧል፡፡ እንደሚታወቀው አርብቶ አደር አካባቢዎች ከጎረቤት ሀገራት ጭምር የተለያዩ ግብይቶች ያሉበት ነው፡፡ በተለይ የቁም እንስሳት በተለየ ሁኔታ ወደ ገበያ የሚቀርቡበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ የሚታየው ችግር ከሕገወጥ ንግድ ጋር ተያይዞ ኅብረተሰቡ ሊያገኝ ይገባ የነበረውን ጥቅም እና እንደ ሀገር ልናገኝ የሚገባውን ውጪ ምንዛሪ ግኝትም የሚቀንስ በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በዚህ ላይ መሥራት እንፈልጋለን፡፡ >> ብለዋል፡፡

ፕሮጅክቱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመሆን በፈጸመው የሦስትዮሽ ስምምነት በመተባባር የሚተገብረው ነው፡፡ የሚተገበረውም በአፋር፣ ሶማሊ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ምዕራብ ክልሎች ነው፡፡ ይህም አርብቶ አደሮች የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነታቸውን ለማሳደግና የቁም እንስሳት ንግድ በአፍሪካ ቀንድ እንዲስፋፋ የሚግዝ ነው፡፡ የሚያተኩረውም በእንስሳት ሀብት ልማት (Livestock) ላይ ሲሆን ቁም እንስሳትን በኤክስፖርት ደረጃ ለማርባት ከዓለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ የሚተገበር ነው፡፡

ይህ አገልግሎትም መስፈርቱን አሟልተው ለሚቀርቡ የግል ባለሀብቶች እና መስፈርቱን አሟልተው ለሚቀርቡ አርብቶ አደር ወጣቶችና ሴቶች ኅብረት ስራ ማኅበራት በሚሰጥ የፋይናነስ አገልግሎት እንደሚሆንም ባንኩ አረጋግጧል፡፡ ለዚህ አገልግሎትም ባንኩ ቁም እንስሳት ጨምሮ ተገቢ ያላቸውን ተንቀሳቃሽ ማስያዣዎች የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

## ልዩ ትኩረት የሚሻው ዘርፍ



### የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ትኩረት ሰጥቶ የፋይናንሲንግ ሴክተር ከሚሰጣቸው ዘርፎች አንዱና ዋነኛው የግብርና ዘርፍ ነው፡፡

ግብርና ዘርፍ በምግብ ራስን ለመቻል፣ ለውጪ ገበያ በማቅረብ ምንዛሬ ለማግኘት፣ ለግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ደግሞ ግብዓት ለማቅረብ፣ እጅግ በከፍተኛ ቁጥር የሀገሪቱን የሰው ኃይል የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የተፈጥሮ ሥነ ምኅዳር ለመጠበቅ የሚያስችል ዘርፍ በመሆኑ በመንግሥትም ዘንድ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም የግብርና ዘርፍ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከተመሠረተበት 1901 ዓ.ም ጀምሮ ቅድሚያ የሚሰጠው ዘርፍ ነው፡፡ ግብርና ከነበረበት ልማዳዊ አሠራር ወጥቶ ዘመናዊ በሆነና መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት በሚስችል መንገድ እንዲካሔድ ልማት ባንክ የበኩሉን ድርሻ ሲወጣ ቆይቷል፡፡ በተሠሩ ሰፊ ሥራዎች በሁሉም የግብርና ዘርፎች አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አሁንም የነበሩ ጠንካራ ጅምሮችን ለማስቀጠል ክፍተቶችን ለመሙላት በሚያስችል መንገድ የግብርናውን ዘርፍ ለመደገፍ የሪፎርም ሥራዎችን እያከናወነ ነው፡፡ ባለፉት ሦስት ዓመታትም የተመዘገቡት ውጤቶች በዘርፉ አበረታች ለውጥ መምጣቱን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በፕሮጀክት ፋይናንስ ለዘመናዊ እና ሰፋፊ እርሻ ልማቶች (Modern and Commercial Agriculture)፣ ለእንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት (Dairy, Poultry and Fishery Farms) ለተሰማሩ ኢንቨስተሮች እንደየ ብድር ጥያቄያቸው አዲስ ብድር፣ የተጨማሪ ብድር፣ የማስፋፍያ ብድር እና

የሥራ ማስኬጃ ብድር ያቀርባል። እንዲሁም በሊዝ ፋይናንሲንግ ለግብርና ሜካናይዜሽን የማሽነሪ ድጋፍ በማድረግ የበኩሉን አስተዋጾ እያደረገ ይገኛል። ባንኩ የወጪ ንግድ በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት፤ ከውጭ የሚገባ ምርትን ለሚተኩ ምርቶች የፋይናንስ እገዛ በማድረግ የውጭ ምንዛሪን ለመቆጠብ በሚደረገው ጥረት ላይ እየተሳተፈ ይገኛል፤ እንዲሁም ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት፤ ለመንግሥት የታክስ ምንጭን በማስፋት፤ ወዘተ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል።

3ኛውን የግብርና ግብዓቶች ኤክስፖ መነሻ በማድረግ "በፋይናንስ የተደገፈ ግብርና ለኢትዮጵያ ብልፅግና" በሚል መሪ ቃል በተዘጋጀው የፓናል ውይይት ተገኝተው ጽሑፍ ያቀረቡት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የኮርፖሬት ግብርና ፋይናንሲንግ ክላስተር ም/ፕሬዝዳንት አቶ ጌታቸው ዋቄ በግብርና ረገድ ባለፋት ሦስት ተከታታይ ዓመታት ለመጡ ለውጦች ባንኩ እያካሔደ ያለውን ሪፎርም አስተዋጽኦ ማድረጉን ሲያብራሩ << ባንኩ ያጋጠሙትን ችግሮች በዝርዝር በማጥናት የ5 ዓመት የስትራቴጂ እቅድ ነድፎ መጠነ-ሰፊ ሪፎርም አድርጓል። የስትራቴጂ እቅዱ 7 ምሰሶዎች (Pillars) ያሉት ሲሆን፥ አንዱ ምሰሶ የቢዝነስ ሞዴልና የፖሊሲ ለውጥ ማድረግ ነው። አዲሱ የባንኩ መዋቅር ንዑስ የኢኮኖሚ ዘርፎችን መሠረት በማድረግ እንዲዋቀር የተደረገ ሲሆን፣ የሥራ ክፍሎቹም በዘርፎቹ ዙሪያ እውቀት ባላቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተደራጅተዋል።

የግብርና ሴክተሩን ለማበረታታትም የፖሊሲ ማሻሻያ፣ የወለድ ምጣኔ ማሻሻያ፣ የዲስትሪክቶች የማበደር ጣሪያ ተሻሽሏል።>> ብለዋል።

ባንኩ የግብርና ዘርፍን ለመደገፍ እያደረገ ያለውን አስተዋፅኦ በብዙ መልክ እንደሚገለጽ ያብራሩት አቶ ጌታቸው በዋናነት ከህዳር 27 ቀን 2023 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ባንኩ 11.5% የነበረውን የወለድ ምጣኔ እስከ 7% በማውረድ ለግብርና ዘርፍ የወለድ መጠን ማሻሻያ በማድረግ፤ ፕሮጀክቱንም በዋስትና በመያዝ የብድር ድጋፍ በማቅረብ፤ በዘርፉ ለሚሰማሩ ኢንቨስተሮች የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ፤ የዲስትሪክቶችን የማበደር ጣርያ ከፍ በማድረግ (ከ 45 ሚሊዮን ወደ 100 ሚሊዮን) የግብርና ሜካናይዜሽን ለማስፋፋት እና አዳዲስ ኢንቨስተሮችን ወደ ዘርፉ ለማስገባት በሊዝ ፋይናንሲንግ የማሽነሪ ኪራይ አገልግሎት በመስጠት እየተሠራ ይገኛል>> ብለዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የግብርናውን የፕሮጀክት ፋይናንሲንግ ዘርፍ በቅልጥፍናና በቅርበት ለመደገፍ እንዲቻል ዘርፉን የኮርፖሬት ግብርና ፋይናንሲንግ ክላስተር ምክትል ፕሬዝዳንት የሚመራው ሆኖ በውስጡም 6 - ዳይሬክቶሬቶች (ክሮፕ ፕሮዳክሽን፣ ሆርቲካልቸርና ፎረስተሪ፣ ላይቭ ስቶክ፣ ፖልተሪ፣ ኢንጂነሪንግ፣ ግብርና ፋይናንስ፣ የአፕሬዛል እና የግብርና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬቶች) ተደራጅተው እየሠሩ ነው።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በበጀት ዓመቱ የስድስት ወራት አፈጻጸም 23.63 ቢሊዮን ብር ብድር ያጸደቀ ሲሆን፣ ግብርና ያለው ድርሻ 15 በመቶ ነበር። ግብርና የሀገሪቱን 85 በመቶ ያህል ሰው ኃይል ከመያዙ፣ ከ80 በመቶ ላነሰው ኤክስፖርት ምርት የሚገኘው ከዚሁ ዘርፍ ከመሆኑ ከሀገሪቱ ፍላጎት አንጻር የሚቀርብለት ብድር አሁንም የሚቀረው መሆኑን ባንኩ ያምናል። በዘርፉ የሚሰማሩ ኢንቨስተሮች በከተሞች የሚገኘው ትርፍ ስለሚበልጥባቸው፣ ከተፈጥሮ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አደጋዎች ለዘርፉ ፈተና በመሆኑ፣ ከመሬት አሰጣጥ እና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያሉ ውስንነቶች፤ ከእርሻ ግብአቶች አቅርቦት ጋር የተያያዘ ችግር በዘርፉ የሚሰማሩ ኢንቨስተሮችን እግራቸውን እንዲጎትቱ አድርጓል። በመሆኑም ባንኩ ከወለድ ምጣኔው ከመቀነስ ጀምሮ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችን በመስጠት ዘርፉን በትኩረት እየደገፈ ነው።



# በባንኩ የፋይናንስ አቅርቦት የተቋቋመው የቆርቆሮ ፋብሪካ ተመረቀ

በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የፋይናንስ አቅርቦት የተቋቋመው የቆርቆሮ ፋብሪካ በሀዋሳ ከተማ ተመረቀ። በምርቃት ስነ ስርዓቱ ላይ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀዋሳ ከተማ ከንቲባ ጨምሮ ከፍተኛ የመንግስት አመራሮችና የከተማዋ ባለሃብቶች ተገኝተዋል።

የሐዋሳ ከተማ ከንቲባ አቶ መኩሪያ መርሻዬ በስነ ስርዓቱ ላይ ባደረጉት ንግግር ለክልሉ የመጀመሪያና ብቸኛ የሆነው ቆርቆሮ ፋብሪካ በመከፈቱ የተሰማቸውን ደስታ ገልፀዋል።

ሌሎች ባለሃብቶችም ይህንን ፈለግ በመከተል በተለያዩ ዘርፎች በመሰማራት ራሳቸውንም ከተማዋንም ለማሳደግ ቢመጡ መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነው ብለዋል።





የሲዳማ ክልል ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ሃላፊ አቶ ጎሳዬ ጎዳና በበኩላቸው የፋብሪካው መቋቋም ለከተማዋ እድገት አስተዋፅኦ ከማበርከቱ በላይ ለዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ይህ ፋብሪካ እውን እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ሲያደርግ የነበረውን የኢትዮጵያ ልማት ባንክን አመስግነው ሌሎች ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችም በከተማዋ እውን እንዲሆኑ ከባንኩ ብዙ እንደሚጠብቁ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የኮርፖሬት ኢንዱስትሪ ፋይናንሲግ ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ አዳነ መሃሪ በዚህ ወቅት እንደገለጹት ባንኩ ይህ ፋብሪካ በክልሉ እንዲቋቋም የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረጉን ገልፀዋል፡፡

በተለይም ባለሃብቱ ይህንን ቆርቆሮ ፋብሪካ እውን ለማድረግ ብድሩን ለማግኘት እንዲያሟሉ የሚጠየቁትን ሁሉ በተባለው ጊዜ አሟልተው ለመገኘት ያደረጉት የነበረው ከፍተኛ ጥረት ለውጤት እንዳበቃቸውም ገልፀዋል፡፡

ፋብሪካው በ340 ሚሊየን ብር ካፒታል የተቋቋመ መሆኑን የገለጹት ደግሞ የፋብሪካው ባለቤት አቶ ተስፋዬ ቲሲሶ ናቸው፡፡

ፋብሪካው ከሚያመርተው ቆርቆሮ በተጨማሪ ከ240 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል መፈጠሩን ገልፀው ፋብሪካው እውን እንዲሆን በፋይናንስና በቴክኒክ ከፍተኛ እገዛ ያደረገላቸውን የኢትዮጵያ ልማት ባንክን አመስግነዋል፡፡

# ኤም.ኤን.ኤስ. ማኑፋክቸሪንግ ዓመታዊ የሠራተኞቹን ቀን አከበረ




በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሥር የሚተዳደረው ኤምኤንኤስ ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ዓመታዊ የሠራተኞችን ቀን የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት አከበረ፡፡

በመርሐ ግብሩ ወቅት የድርጅቱ የስድስት ወራት የአፈጻጸም ሪፖርት ቀርቦ ውይይት የተካሄደበት ሲሆን፣ በአፈጻጸማቸው የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ሠራተኞች እውቅናና ሽልማት አበርክቷል፡፡

በመርሐ ግብሩ ማስጀመሪያ ላይ ንግግር ያደረጉት የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ደሳለኝ ፍሬው በውጭ ሀገር ባለሀብቶች እና በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የብድር አቅርቦት የተቋቋመው ድርጅቱ በነበረበት የአሠራር ክፍተት ሳቢያ ለኪሳራ ተዳርጎ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡

በአሁን ሰዓት ባንኩ በወሰደው የማስተካከያ ርምጃ በሙሉ የትግበራ እንቅስቃሴ የሚገኝና አዳዲስ ምርቶችን የሚያመርት ግዙፍ ድርጅት ለመሆን መብቃቱን ገልጸዋል፡፡

ከስድስት ዓመታት በላይ ያለ ስራ ቆመው የነበሩ ከፍተኛ የሀገር ሀብት ፈሶባቸው የገቡ ማሽነሪዎችን ወደ ሥራ በማስገባት በአሁኑ ሰዓት በሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በማምረት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎችና



አባገዳዎች ባንኩ ከረዥም ዓመት ጀምሮ አብሯቸው እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸው በቅርቡ በድርጅቱ በኩል ለአካባቢው ማኅበረሰብ የፈጠረው የሥራ ዕድል ከፍተኛ በመሆኑ አመስግነዋል።

ድርጅቱንም ሆነ ባንኩን እንደራሳችን ሀብት የምንከባከበው ነው ያሉት አባቶች ለአካባቢው ማኅበረሰብ በበጎ አድራጎት፣በንጽህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለወጣቶች የሥራ እድል በመፍጠር ባንኩ ከፍተኛ ሥራ መሥራቱን ገልጸዋል።

በሸገር ከተማ አስተዳደር የለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ አስተዳር የጸጥታ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ዐብይ ምሕረቱ ከባንኩና ከድርጅቱ ጋር በቅርበት በመሥራት ላይ መሆናቸውን ገልጸው በቀጣይም ባንኩ በአካባቢው ለሚሠራቸው ሥራዎች ድጋፋቸው እንደማይለይ ተናግረዋል።

በመጨረሻም በአንደኛ ደረጃ ፣በሁለተኛ ደረጃ እና በሶስተኛ የላቀ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ከ80 በላይ ለሆኑ የድርጅቱ ሰራተኞች የማበረታቻ ሽልማት እውቅና ተሰጥቷል።

## ባንኩ የተሽከርካሪ ድጋፍ አደረገ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለታላቁ የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የተሽከርካሪ ድጋፍ አደረገ።

ባንኩ ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድ በማዘጋጀት ከግንባታ ጀምሮ ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወሳል።

በርክክብ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢ.ል.ባንክ ፕሬዝደንት ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው ባንኩ ከግድቡ ግንባታ ጀምሮ የተለያዩ ድጋፎች ማድረጉን ገልጸው ባንኩ ሁሌም ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ጎን መሆኑን ጠቅሰዋል።





የግድቡ ግንባታ ተጠናቆ ለአገልግሎት እስኪውልም አሁን ከተደገረው የተሽከርካሪ ድጋፍ በተጨማሪ የባንኩ ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

የማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ዶ/ር አረጋዊ በርሄ በበኩላቸው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የግንባታ ሒደቱ ከተጀመረበት ጀምሮ ድጋፉ እንዳልተለያቸው ገልጸዋል፡፡

“ባንኩ በግድቡ ግንባታ ዘርፍ ያደረገው አስተዋጽኦ በቃላት የሚገለጽ አይደለም” ያሉት ኃላፊው <<ለግድቡ ባበረከተው ልክ አልተነገረለትም>> ብለዋል፡፡



በተለይ ቦንድ በማዘጋጀትና ገንዘብ በማሰባሰብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በግንባታው ተሳታፊ እንዲሆን ሂደቱን ሲያግዝ መቆየቱን አስታውሰዋል፡፡

አሁን ያደረገው ድጋፍ ጽሕፈት ቤቱ ተንቀሳቅሶ ለመሥራት ያለበትን የተሽከርካሪ ችግር እንደሚቀርፍ ጠቅሰው ባንኩ ላደረገው ድጋፍ አመስግነዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አ.ኤ.አ

# የ2023/24

## የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የስራ አፈፃጸም

ብር በቢሊዮን

| የአፈጻጸም መለኪያዎች | አ.ኤ.አ 2023/24 | | |
|---|---|---|---|
| | የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት | | |
| | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| 1.1 የብድር ማጽደቅ/መፍቀድ | 23.57 | 23.62 | 100.2% |
| 1.2 የብድር መልቀቅ | 12.35 | 13.15 | 106.5% |
| 1.3 የብድር መሰብሰብ | 7.78 | 6.64 | 85.3% |
| 1.4 ጠቅላላ የብድር ክምችት | 84.36 | 83.70 | 99.2% |
| 1.5 የተበላሸ የብድር መጠን | 7.17 | 10.00 | 71.7% |
| 1.6 የተበላሸ የብድር ምጣኔ | 8.51% | 11.95% | 71.2% |
| 1.7 የተጣራ የትርፍ መጠን | 3.03 | 1.47 | 48.4% |

- ባንኩ በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ከደንበኞች ለሚቀርቡ እና የባንኩን የብድር መስፈርት የሚያሟሉ የብድር ጥያቄዎችን ተቀብሎ ለማጽደቅ ብር 23.57 ቢሊዮን ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ብር 23.62 ቢሊዮን በማድረስ የዕቅዱን 100.2 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ፡፡
- ባንኩ በግማሽ ዓመት ለደንበኞቹ ብድር ለመልቀቅ ብር 12.35 ቢሊዮን ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ብር 13.15 ቢሊዮን በማድረስ የዕቅዱን 106.5 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል፡፡
- ባንኩ በግማሽ ዓመት ብር 7.17 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ብር 6.64 ቢሊዮን በማድረስ የዕቅዱን 85.3 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ፡፡
- በግማሽ ዓመት የተበላሸ የብድር መጠንን ወደ ብር 7.17 ቢሊዮን ዝቅ ለማድረግ ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ወደ ብር 10.00 ቢሊዮን የጨመረ ሲሆን ይህም የዕቅዱን 71.7 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ፡፡
- ባንኩ በግማሽ ዓመት ከጠቅላላ የብድር ክምችት ውስጥ የተበላሸ የብድር ምጣኔውን ወደ 8.51 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ያቀደ ሲሆን ክንውኑም 11.95 በመቶ ያደገ ሲሆን የዕቅዱን 71.2 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ፡፡
- ባንኩ በግማሽ ዓመት ጠቅላላ የብድር ክምችት መጠኑን ብር 84.36 ቢሊዮን ለማድረስ ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ብር 83.70 ቢሊዮን በማድረስ የዕቅዱን 99.2 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ፡፡

# ማስታወሻ





አቶ ቢተው አስፋው



አቶ ያሬድ ከልካይ



አቶ አሰፋ ኃይለማርያም

## የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በቅርቡ ሕይወታቸውን በመኪና አደጋ ያጡ ትጉኃን ሠራተኞቹን ሲያስታውስ በታላቅ ሐዘን ነው።

- **አቶ ቢተው አስፋው**

  በአካውንቲንግ የባችልር ዲግሪ የነበራቸው፣ በባንኩ 10 ዓመታት ከሰባት ወራት ያገለገሉና ህይወታቸው አስካለፈበት የካቲት 25 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የሁመራ ዲስትሪክት ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጅ ነበሩ።

- **አቶ ያሬድ ከልካይ**

  በቢዝነስ አድምንስትሬሽን የማስትርስ ዲግሪ የነበራቸው፣ በባንኩ ሰባት ዓመታት ከአሥራ አንድ ወራት ያገለገሉ እና ሕይወታቸው እስካለፈበት የካቲት 25 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የዳንሻ ቅርንጫፍ የብድር ትንተና የቡድን ስራ አስኪያጅ ነበሩ።

- **አቶ አሰፋ ኃይለማርያም**

  የሰርተፍኬት ምሩቅ ሆነው ባንኩን ለስምንት ዓመት ከአራት ወራት ያገለገሉ ሲሆን፣ ሕይወታቸው እስካለፈበት የካቲት 25 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በሁመራ ቅርንጫፍ ሲኒየር አሽከርካሪ ነበሩ።

እነዚህ የባንኩ ሠራተኞች የታርጋ ቁጥሩ ኮድ 3- ኢት 70110 የመሥሪያ ቤታችን ንብረት በሆነ ተሽከርካሪ ከጎንደር ወደ ሁመራ ለሥራ ጉዳይ ሲጓዙ አርማጭሆ ወረዳ ልዩ ስሙ ትክል ድንጋይ በሚባል አካባቢ በገጠማቸው የመኪና አደጋ ሕይወታቸው ማለፉን ስናስታውስ በመሪር ሐዘን ነው።

በተጨማሪም ከእነዚህ ትጉኃን የባንኩ ሠራተኞች በሕይወት ከማለፋቸው ከወራት በፊት ሕይወቱን ያጣውን፣ በፕሮጀክት ማኔጅመንት ማስተርስ ዲግሪ የነበረው፣ በባንኩ ለስምንት ዓመታት ያገለገለ፣ ሕይወቱ እስካለፈበት ቀን ድረስ በደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት በሲኒየር አካውንታንትነት ሲያገለግል የነበረውን አቶ ተላከ አስማረን ስናስታውስ በባንኩ ሠራተኛነት ያሳይ የነበረውን ትጋትና ንቃት የማይረሳ መሆኑን በማሰብ ነው።



አቶ ተላከ አስማረን

የሁሉንም ነፍስ በአጸደ ገነት እንዲያሳርፍ የባንኩ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣ የማኔጅመንት አባላትና የመላው ሠራተኞች ምኞት ነው።

ጆሴፍ ብሮዝ ቲቶ መንገድ
+251 11 551 1606
+251 11 551 1188/89
1900

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
የልማት አጋርዎ !